ታኅሣሥ ፱ ፳፻፲

# ኢትዮጵያ ሃገራችን ነጻነት ጥያቄያችን የትብብር ቀጣይ ጥሪ

ለጋራ ግንዛቤያችን መገለጫ ያደረግነው ዓርዕስት፣ከርዕስነቱ በላይ በውስጣችን የሚንቦለቦለውንና የሚንቀለቀለውን ኢትዮጵያዊነትንና የነጻነት ጥማታችንን ለመግለጽ ነው።

በአጥንት ፍላጭ፣በስጋ ቁራጭ፣በደም እንጥፍጣፊ፣ለዘመናት ተከብራ የኖረች አገራችን ዛሬ የህዝብ ድምጽ የሌላቸው ብኩርነታቸውን ለግል ጥቅም የለወጡ የባዕድ ቅጥረኞች ሀገሪቱን ከካርታ ህዝቧን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ባኰበኰቡበት ወቅት ጥያቄያቸውን ነጻነት ላሉና የተባበሩ አገር ወዳድ ሃይላትን ለማበር ስንል ነው፤በአለም ዙሪያ ያለነው የተግባር ሃይሎች ለህብረታችን መሰረት የጣልነው።

ብዙውን አሳስሮ ፣አቁስሎ፣በርካታውን ገድሎ፣ ብዙ መስዋዕትነትን አስከፍሎ ዛሬም የነጻነቱ ጥያቄ ተንከባሎ እኛ ጋር ሲደርስ የታሪክ ጥላ ነውና ላንሸሸው ተማምለን በጋራ አብረን እነሆ ለነጻነቱ ትግል የራሳችንን አሻራ ለማሳረፍ በጥሩ ተግባብተናል።

በተለይ ሰሞኑን በሃገር ቤት በይፋ የሚንቀሳቀሱ ዘጠኝ የህብረብሄርና የብሄር ድርጅቶች ለጋራ ኢትዮጵያችን ነጻነት ተባበርን ሲሉን በሀሳብም ሆነ በቁስ ለመርዳት የተነሳንበት ምክንያት ስለተባበሩ ብቻ ሳይሆን ከጎናቸው የቆምነው፤ የነጻነት ጥያቄያችንን ስላልሰባበሩም ጭምር ነው።

ከዋሽንግተን ዲሲ የጋራ ግብረሃይል ተነስቶ ሰሜን አሜሪካ በርካታ ግዛቶችን አጠቃሎ ከአውሮፓ እስከ አፍሪካ ዞሮ የገጠመው አለም አቀፍ ግብረሃይል ባሳለፍነው ሳምንት በርካታ ተወካዮቹ ባደረግነው ጥልቅ ወቅታዊ ዉይይት ኢትዮጵያ ሃገራችን ነጻነት ጥያቄያችን በሚለው መሪ መፈክር ተስማምተናል። ለዚህም ከዚህ ቀደም የተከፈሉ መስዋዕትነቶችን ክብር ሳንነሳ፤ ያሳለፍነውን ወርሃ ህዳርን ለነጻነት ህዝባዊ እንቢተኝነት ለማድረግ ያበሩት ዘጠኝ ፓርቲዎች እንከፍላለን ያሉትን የነጻነት ዋጋ ባደባባይ ስለከፈሉ ያለንን አድናቆት እየቸርን ወደፊትም ለሚያደርጉት ህዝባዊ ፣ሃገራዊና ተግባራዊ ትግል እንደትናንቱ ዛሬም ፣ነገም ከጎናቸው እንደምንቆም ባደባባይ እንገልጻለን።

በማጠቃለያም ለትብብሩ ትብብር ላደረጉት ሁሉ አድናቆታችንን እየገለጽን ኢትዮጵያ ሃገራችን ነጻነት ጥያቄያችን የሚሉ ሃገር ወዳድ ሃይሎች ይበልጡኑ እንዲተባበሩ አለም አቀፉ ግብረሃይል ወገናዊ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ላልተሸራረፈ ነጻነት እናብር!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም በክብር ትኖራለች!!!

አለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ግብረሃይል

ለማንኛውም መረጃ dcjointtaskforce@gmail.com ወይም 571 403 2474